**የአማራ ፋኖ በጎጃም**

**ወታደራዊ መምሪያ**

**Amhara Fano In Gojjam**

**Army Command**

---

*ቀን 22.07.2017 ዓ.ም*

# የዘመቻ አንድነት ለሚዲያ የሚውል ጥቅል ሪፖርት

**መግቢያ፡-** ይህ ፅሁፍ ስለ ዘመቻ አንድነት ውጤት ለሚዲያ አገልግሎት እንዲሁም ለህዝባችን እና ለደጋፊዎቻችን የሚቀርብ ዝርዝር እሪፖርት ነው፡፡ እሪፖርቱ በሶስት ንዑስ ርዕስ የተከፋፈል ሲሆን የዘመቻው ስያሜ አሰጣጥን ጨምሮ ዘመቻ አንድነት በየትቀጠና እንዲሁም መቸ እና በማን ተግባራዊ እንደሚሆን የሚያብራራ ግልፅ እና ተጨባጭ መረጃዎችን ያጠቃለለ አጭር እሪፖርት ሲሆን ትርፍ እና ኪሳራዎችን የምናሳይበት ፣የምንተነትንበት ፍፁም የሆነ ከብሮፖጋንዳ ትርፍ የጸዳ የተተገበረ፣የተደረገ፣ የሆነውን ሁሉ በእውነታ ላይ የተመሰረተ ግልፅ ትንታኔ ነው፡፡

ይህ እሪፖርት ከነበረ የአውደ ውጊያ የቀን ውሎአችን ከሰራዊታችን ተጋድሎ እና ካስገኘነው አኩሪ ገድል ውስጥ ጎልተው የሚታዩ እና በጠላት ላይ ከባድ የሚባል ኪሳራ ያደረሱትን የዘመቻ ውጤቶች ብቻ በውጊያ እሪፖርት ከታችኛው የሰራዊታች አመራሮች ያገኘናቸውን መረጃዎች ሳንጨምር ጨምቀን ያዘጋጀናቸው እሪፖርቶች ናቸው፡፡

ለሚድያ አገልግሎት መዋል የሌለብቸው የተሰነዱ ሚስጥራዊ ዘመቻዎችን እና ጥቃቅን ድሎቻችንን ይህ እሪፖርት አያካትትም፡፡

## የዘመቻ አንድነት ምንድን ነው፡-

ዘመቻ አንድነት ከጥሬ ትርጉሙ መረዳት እንደሚቻለው የጋራ ጠላታችንን ማለትም እንደ ህዝብ የአማራን ህዝብ ለማጥፋት እና ለማንበርከክ በእብሪት በአፅመ እርስቶቻችን የገባውን ጠላት የአብይ አህመድ ቅጥረኛ ሰራዊት በአንድነት፣ በጋራሃሳብ፣በጋራ ጥምር ተኩስ፣በጋራ ማጥቃት፣በጋራ እውቀት እና ልምድ፣በጋራ አፈሙዝ፣ በተቀናጀ፣በተናበበ፣በተሳሰረ እና በተባበረ ክንዳችች የመከላከል ምሽግ መስርቶ የተቀመጠን ጠላት በሁሉም የአማራ ምድር አንድ በመሆን መቀጥቀጥ እና መምታት ነው፡፡

ይህ ዘመቻ አንድ ድርጅት ለመፍጠር የሁሉንም ቀጠና በሰብሳቢነት ደረጃ ያሉ አመራሮች ውይይት ላይ ባሉበት እና የህዝባችን የአንድነት ጥያቄ አዎንታዊ ጫና በፈጠረበት በተቃራኒው ደግሞ ጠላቶቻችን ፋኖ አንድነት የለውም፣አንድ መሆን አይችልም፣ፋኖ የሰፈር አደረጃጀት ነው ያለው፣የሚል ጥቅል ግምገማ ባደረጉበት በዚህ ወቅት ከህዝባችን ስቃይ እና መከራ ከሰራዊታችን የቀን ተቀን መስዋትነት የሚበልጥ እንደሌለ እና ሁሉንም የማድረግ አቅም በእጃችን ላይ እንዳለ ለሁሉም ማስተማር በሚችል ስያሜ ውጊያ ማድረግ እንደምንችል አሳይተን አንድነት መፍጠር ደግሞ መብት ሳይሆን ግዴታ እንደሆነ ለማስገንዘብም ጭምር የመሪዎቻችንን ድካም የሚያቃልል ዘመቻ እንድነት በሁሉም ቀጠና ያለን ወታደራዊ አዛዦች እና ዘመቻ መሪዎችን ጋር በመሆን የተዘጋጀ እቅድ ነበር፡፡ዘመቻው በቀን 10/07/2017ዓ.ም ንጋት 11፡00 ሰዓት በሁሉም የጠላት ምሽጎች ላይ ማጥቃት የተደረገ ሲሆን የዘመቻው መጨረሻ በጠላት ላይ በምናደርሰው ኪሳራ የሚወሰን እንደሚሆን በእቅዳችን ላይ ተካቷል፡፡

---

ከስያሜውም አንፃር አንድነትሃይል ነው፣አንድነት ጉልበት ነው፣አንድነት የአሸናፊነት ግዙፉ ሚሳኤላችን እንደሆነ ያገኘነው የድል ውጤት አስተምሮናል። ይህን ማድረግ በመቻላችን ህዝባችን መደሰቱ ብቻም ሳይሆን ጠላታችን በድንጋጤ እና በፍርሃት፣በጭንቀት ውስጥ ሆኖ አራባና ቆቦ መግለጫዎችን ሲያወጣም አይተናል። እድሜ ጠገብ ምርኮኛ የሰራዊት ጀኔራሎች የማያልሙትን ታሪካዊ ውጊያ አድርገን በዘመቻው የመከላከል አቅም እንኳን ያላገኘው የአብይ ተቀላቢ ሰራዊት ፋኖን ከትግራይ ወታደራዊ አመራሮች ጋር ደባለቀው መግለጫ እንድያወጡ አድርገናቸዋል። በዚህ መግለጫቸው ሁላችንም የሳቅን ቢሆንም ከአንድ ራሱን ኢንተርናሽናል የሚሊተሪ ተቋም አድርጎ ከሚቆጥር መከላከያ ከሚባለው ተቋም እና አመራር እንደዚህ አይነት የማይገጣጠም እና ከጉዳዩ ጋር የማይገናኙ መግለጫዎችን ስንመለከት እንደህዝብ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ሃገር ኢትዮጵያ ሃፍረት ይሰማታል።እያልሁኝ በዘመቻው ያገነናቸውን ድሎች እንደሚከተለው አብራራለሁ።

**በዘመቻ አንድነት የተገኙ ድሎች፡-**

***በዘመቻ አንድነት የ12 ቀን ጥቅል ተጋድሎ***

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ1ኛ ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- ሻለቃ አንሙት ብርጌድ-2 ጊዜ
- ባህር ዳር ብርጌድ-3 ጊዜ
- የጣናው መብረቅ ብርጌድ 3-ጊዜ
- ኮሎኔል ታደሰ ሙሉነህ ብርጌድ 5-ጊዜ ውጊያ ያደረጉ ሲሆን

በዚህ ዘመቻ የ1ኛ ክፍለ ጦር ውጊያ ያደረገባቸው ቀጠናዎች አዴት፣ምላጭበር፣ዴንሳ ባታ፣መራዊ፣ገርጨጭ፣ዳጊ፣አማሪት፣ብራቃት፣መኮድ፣መቶካብ፣አየር ሃይል፣ቻይና ካንፕ፣አባይ ማዶ፣እንጨት ተራ፣አቡነ ሃራ፣ሬም እና ባህርዳር ቀበሌ 11 ዉጊያ የተረገባቸው ቦታዎች ሲሆኑ

ከነዚህ ቦታዎች ውስጥ ውጊያ የተደጋገመባቸው ቦታዎች

- አዴት 2 ጊዜ
- ዳጊ 2 ጊዜ
- ገርጨጭ 3 ጊዜ
- መራዊ 2 ጊዜ
- አማሪት 2 ጊዜ

በአጠቃላይ የአማራ ፋኖ በጎጃም 1ኛ ክፍለ ጦር በዘመቻ አንድነት 13 አውደ ውጊያዎች አድርጓል።

---

በዚህ ክፍለጦር የተገኘ የምርኮ ብዛት

- 16 የጠላት ሃይል የተማረከ 1ዱ የኮማንደር ማዕረግ ያለው ነው
- 1 ፓትሮል

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 259 የጠላት ሃይል ተሰዋ
- 135 የጠላት ሃይል የቆሰለ

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 01 ዲሽቃ ከጥቅም ውጭ የሆነ
- 31 ክላሽ የተማረከ
- 10800 የክላሽ ጥይት የተማረከ
- 02 መገናኛ የተማረከ
- 1 ፓትሮል የተቃጠለ

በዚህ ዘመቻ የተገኘው የድል ውጤት ጠላት ላይ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ ያደረስን ሲሆን አማራት ከተማን መቆጣጠር ተችሏል።

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ2ኛ(ተፈራ ዳምጤ) ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- መብረቁ ብርጌድ - 5 ጊዜ
- ዮሐንስ አለማየሁ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ደጋ ዳሞት ብርጌድ - 1 ጊዜ
- መዝገቡ ዋለልኝ ብርጌድ - 1 ጊዜ
- መዝገቡ ጮቄ ብርጌድ - 1 ጊዜ ዉጊያ አድርገዋል።

በ2ኛ ተፈራ ዳምጤ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

ሞጣ ከተማ፣ደጋ ዳሞት ፈረስ ቤት ከተማ፣ቢቡኝ ወይን ውሃ እና ድጎ ከተማ፣ሰዴ ከተማ፣ጎንጅ ከተማ፣ዋሸራ ከተማ፣አራጢ ጫካ ሲሆኑ በድግግሞሽ ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

- ሞጣ 3 ጊዜ
- አራጢ 2 ጊዜ

---

በአጠቃላይ ይህ ክፍለ ጦር 10 ውጊያዎችን ማድረግ ችሏል፡፡

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 102 የጠላት ሃይል የተሰዋ
- 110 የጠላት ሃይል የቆሰለ

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 01 ዲሽቃ ከጥቅም ውጭ የሆነ
- 7 ክላሽ የተማረከ

የ2ተኛ ተፈራ ዳምጤ ክፍለጦር ያስገኛቸው የድል ውጤቶች በጠላት ላይ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ የቻለ ሲሆን ዋሸራ ከተማን መቆጣጠር ተችሏል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ3ኛ(ጎጃም አገው ምድር) ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- ስሜነህ ደስታ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- ዘንገና ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ጊዮን ብርጌድ - 3 ጊዜ
- አቤ ጉበኛ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- ኤፍሬም አጥናፉ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ቢትወደድ መንገሻ ጀንበሬ ብርጌድ - 3 ጊዜ ሲሆን

በዚህ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

አሸፋ፣ወርቅ ሜዳ፣ደብረ ዘይት፣መልከታ፣ቲሊሊ፣ሊበን፣ቁንዝላ፣ዝብስት፣ዳጊ፣ከ1ኛ ክፍለ ጦር ጋር በመጣመር አሹዳ፣ፋግታ እና አዲስ ቅዳም፣ዳንግላ፣ዘለሳ ሲሆኑ

በድግግሞሽ ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

- አሸፋ 2 ጊዜ
- ሊበን 2 ጊዜ
- መልከታ 2 ጊዜ

በአጠቃላይ የአማራ ፋኖ በጎጃም 3ተኛ የጎጃም አገው ምድር ክፍለ ጦር 16 ዉጊያዎችን ያደረገ ሲሆን

የምርኮ ብዛት - 22 የጠላት ሃይል የተማረከ

- 01 ፓትሮል የተማረከ

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 149 የጠላት ሃይል የተሰዋ
- 81 የጠላት ሃይል የቆሰለ
- 1 ኮሎኔል አባተ የተባለ አዋጊ እና 1 ለጊዜው ስሙ ያልተረጋገጠ አዋጊ ተደምስሰዋል፡፡

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 01 ዲሽቃ የተማረከ
- 03 ብሬን የተማረከ
- 01 ስናይፐር የተማረከ
- 86 ክላሽ የተማረከ
- 6 ሽጉጥ የተማረከ
- 10,000 የክላሽ ጥይት የተማረከ
- 2 መገናኛ የተማረከ
- 2 ፓትሮል የተቃጠለ
- 1 ዙ-23 ከጥቅም ውጭ የሆነ
- 2 የጠላት ሞተር የተቃጠለ
- 140,000 ብር ከኮሎኔል አባተ ኪስ የተማረከ
- 02 ኮምፒዩተር የተማረከ

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት በጠላት ላይ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ የተቻለ ሲሆን አሸፋ ከተማን መቆጣጠር ተችሏል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ4ኛ(ጃዊ) ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- ኤፍሬም ብርጌድ
- ደምስ ብርጌድ
- በላይ ብርጌድ
- ነጋሽ ብርጌድ
- መተከል ጣና በለስ ብርጌድ
- ናሁሰናይ ብርጌድ
- መብረቁ ብርጌድ

---

- ክንድዬ ብርጌድ

ይህ ክፍለ ጦር በዚህ ዘመቻ 6 አውደ ውጊያዎችን ማድረግ ችሏል፡፡

በዚህ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

መንደር 22፣መንደር 24፣መንደር 17፣ወርቅ ሜዳ፣ማንዱራ፣ጃዊ ፈንድቃ ሲሆን

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 24 የጠላት ሀይል የተሰዋ
- 11 የጠላት ሃይል ቁስለኛ

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት በጠላት ሃይል ላይ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ5ኛ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲክም ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- ገረመው ወንዳወክ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- አረንዛው ዳሞት ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ደጃች አሰቦ ብርጌድ - 5 ጊዜ
- ወንበርማ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- ጓጉሳ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ወርቅአባይ ብርጌድ - 3 ጊዜ

በዚህ ክፍለጦር ውጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች ብርአዳማ፣ሸንዲ፣ቡሬ፣ቁጭ፣ገነት አቦ፣ጅጋ፣አለፋ፣አዘና ሲሆኑ ተደጋጋሚ ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

- ብር አዳማ 2 ጊዜ
- ገነት አቦ 3 ጊዜ ሲሆን

በአጠቃላይ የ5ተኛ ክፍለ ጦር 18 አውደ ዉጊያዎችን ማድረግ ችለዋል፡፡

የምርኮ ብዛት

- 5 የጠላት ሃይል የተማረከ

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 185 የጠላት ሃይል የተሰዋ

---

- 104 የጠላት ሃይል የቆሰለ

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 49 ክላሽ
- 06 የቃታ ብረት
- 01 እንፎርቷ
- 1000 የእንፎርቷ ጥይት
- 2 ጆንያ ከስክስ ጫማ
- 1 ካሶኒ ሙሉ ሬሽን
- 7000 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ
- 5600 የክላሽ ጥይት
- 10 ኩንታል ከህዝብ የዘረፉት ቡና መማረክ ተችሏል፡፡

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት

- ብር አዳማ
- አለፋ እና ቁጭ ከተማን መቆጣጠር ችለናል፡፡
- 421 ወንድ
- 05 ሴት አንዷ ከነ 2 ህፃናት ልጆቿ ንፁሃን እስረኞችን ያስለቀቅን ሲሆን ያዩ ጋጉሳ ወረዳ የብልፅግና መዋቅር ተበትኗል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ6ኛ የቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- በላይ ዘለቀ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ኢንጅነር ክበር ተመስጌን - 2 ጊዜ
- ስናን አባ ጅሜ ብርጌድ - 1 ጊዜ
- ቀስተ ደመና ብርጌድ - 2 ጊዜ
- በረኸኛው ጅበላ ሙተራ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ብርጌድ - 1 ጊዜ ሲሆን

በዚህ ክፍለጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች ደብረ ማርቆስ ማረሚያ ቤት፣ደብረ ማርቆስ ውሃ ጋን፣ደብረ ማርቆስ 15ኛ ሻለቃ፣ረቡዕ ገበያ፣አማኑኤል፣ደንበጫ፣የጨረቃ፣መጋለ ቡሬ፣ደብረ ኤልያስ ሲሆን በድግግሞሽ ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

- አማኑኤል 2 ጊዜ ተዋግተናል፡፡

---

በአጠቃላይ የቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉስ ክፍለ ጦር 10 አውደ ዉጊያዎችን ማድረግ ችለዋል።

የምርኮ ብዛት - 19 የጠላት ሃይል የተማረከ

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 125 የጠላት ሃይል ከ03 አመራር ጋር ተደምስሰዋል
- 45 የጠላት ሃይል ቁስለኛ ማድረግ ተችሏል።

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 04 ብሬን የተማረከ
- 01 ስናይፐር የተማረከ
- 84 ክላሽ የተማረከ
- 3 መገናኛ ሬዲዮ የተማረከ
- 03 የወገብ ትጥቅ የተማረከ
- 11700 ጥይት የተማረከ

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት በጠላት ላይ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ የተቻለ ሲሆን የጨረቃ ከተማን መቆጣጠር ተችሏል።

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ7ኛ የአዲስ አለማየሁ ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- አብራጅት ብርጌድ - 4 ጊዜ
- ተድላ ጓሉ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- አባይ ብርጌድ - 3 ጊዜ
- መብረቁ ብርጌድ - 3 ጊዜ

በዚህ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

ማርቆስ ከተማ፣አንበር፣ሉማሜ፣ወጀል፣ንፋሳም፣ኮርክ፣ጃማ፣እነሞጨራ፣የጁቤ መገንጠያ፣ሰጋ በድግግሞሽ ዉጊያ የነበረባቸው ቦታዎች

- ኮርክ 3 ጊዜ
- ወጀል 2 ጊዜ
- አንበር 2 ጊዜ

---

በአጠቃላይ የአዲስ አለማየሁ ክፍለ ጦር 13 አውደ ዉጊያዎችን ማድረግ ችሏል፡፡

የምርኮ ብዛት - 2 የጠላት ሃይል መማረክ ተችሏል፡፡

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 106 የጠላት ሃይል የተሰዋ
- 95 የጠላት ሃይል ቁስለኛ

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 02 ክላሽ የተማረከ
- 02 ትጥቅ የተማረከ
- 300 ጥይት የተማረከ

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት በጠላት ላይ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ8ኛ በላይ ዘለቀ ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- አባ ኮስትር ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ዛንበርሃ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ደባይጮቂ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ሶማ ብርጌድ - 2 ጊዜ
- ሽፈራው ገርባው ብርጌድ - 3 ጊዜ

በዚህ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

ደብረ ወርቅ፣ቢቸና፣የትመን፣ቁይ፣ጉበያ፣የዶሃ፣መርገጭ፣ወይራ፣ሳፈቅዳ ሲሆን በድግግሞሽ ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች

- የዶሃ 3 ጊዜ
- ቁይ 2 ጊዜ
- ቢቸና 2 ጊዜ

በአጠቃላይ የበላይ ዘለቀ ክፍለ ጦር 11 አውደ ዉጊያዎችን ማድረግ ችለዋል፡፡

የምርኮ ብዛት 13 የተላት ሃይል የተማረከ

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

---

- 86 የጠላት ሃይል የተሰዋ
- 80 የጠላት ሃይል የቆሰለ

በጠላት ላይ የደረሰ ቁሳዊ ኪሳራ

- 12 ክላሽ የተማረከ
- 03 የወገብ ትጥቅ የተማረከ
- 4700 ጥይት ተማርኳል፡፡

በዘመቻው የተገኘ የድል ውጤት በጠላት ላይ ቁሳዊ እና ሰብዓዊ ኪሰራ ማድረስ ተችሏል፡፡

## የአማራ ፋኖ በጎጃም የ9ነኛ ሳሙኤል አወቀ ክፍለ ጦር

በዘመቻው የተሳተፉ ብርጌዶችና ያደረጉት የውጊያ ብዛት

- አባይ ሽለቆ ብርጌድ - 4 ጊዜ
- አረንዛው ጎንቻ ብርጌድ - 2 ጊዜ

በዚህ ክፍለ ጦር ዉጊያ የተደረገባቸው ቦታዎች ድቦ፣መርጦለማርያም፣ግንደወይን፣በአርጃኖ ሲሆን

በአጠቃላይ የሳሙኤል አወቀ ክፍለ ጦር 6 አውደ ዉጊያዎችን ማድረግ ችለዋል፡፡

በጠላት ላይ የደረሰ ሰብዓዊ ኪሳራ

- 27 የጠላት ሃይል የተሰዋ
- በቁጥር የልተረጋገጠ ቁስለኛ ማድረግ ተችሏል፡፡

በዘመቻው የተገኘ የድል ዉጤት በጠላት ሃይል ላይ ቁሳዊ እና ሰዋዊ ኪሳራ ማድረስ ተችሏል፡፡

## በጎጃም ግንባር አጠቃላይ የዘመቻ አንድነት ድሎችና ቁጥራዊ መረጃዎች

ከመጋቢት 10/2017 ዓ/ም እስከ መጋቢት 21/2017 ዓ/ም ድረስ በዘመቻ አንድነት የተመዘገቡ ድሎች እና ቁጥራዊ መረጃዎች

በጎጃም ግንባር

- ✓ 101 አውደ ዉጊያዎች ተካሂደዋል፡፡
- ✓ 82 ልዩ ልዩ ቦታዎች ላይ ዉጊያ አድርገናል፡፡
- ✓ 19 አውደ ዉጊያዎች የተደረጉት በተመሳሳይ ቦታ ነው፡፡
- ✓ በዚህ ዉጊያ በ2 ቦታዎች ላይ ሞርተር- 82 የተጠቀምን ሲሆን 12 ቀን የፈጀ ዉጊያ ካሉን 9 ክፍለ ጦሮች 9ጠኙንም ክፍለ ጦሮች በዉጊያው አሰልፈናል፡፡

በአጠቃላይ በዘመቻ አንድነት በጠላት ላይ የደረሰ ኪሳራ

- የተደመሰሰ የጠላት ሃይል 1063 ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አዋጊ ኮሎኔሎች፣የሚኒሻ እና የአድማ ብተና አመራሮች ይገኙበታል፡፡
- በዚህ ዘመቻ የቆሰለ የጠላት ሃይል 661 ሲሆን የተማረኩት ደግሞ 77 ናቸው 1 የጠላት ኮማንደርም ይገኝበታል፡፡

በዚህ ዘመቻ ከጠላት የተማረኩ ንብረቶች

- 01 ዲሽቃ
- 07 ብሬን
- 02 ስናይፐር
- 271 ክላሽ
- 06 ሽጉጥ
- 07 መገናኛ ሬዲዮ
- 55 የእጅ ቦንብ
- 44,100 ልዩ ልዩ ተተኳሽ ጥይቶች
- 03 ፓትሮል
- 02 የጠላት ኮምፒዩተር
- 10 ኩንታል ከህዝብ የተዘረፈ ቡና
- 140,000 ብር ከኮሎኔሉ ኪስ የተማረከ
- 7000 ኩንታል ከህዝብ የተደበቀ የአፈር ማዳበሪያ

በዘመቻ አንድነት ከጠላት ነፃ የወጡ ከተሞች እና የጠላት ይዞታዎች

- ✓ አለፋ
- ✓ ቁጭ
- ✓ ብርአዳማ
- ✓ አማሪት
- ✓ ዋሸራ
- ✓ አሸፋ በዘመቻው ነፃ የወጡ ቦታዎች ናቸው፡፡

**የአማራ ፋኖ በጎጃም**

**ወታደራዊ መምሪያ**

**Amhara Fano In Gojjam**

**Army Command**

---

**ማጠቃለያ፡-** በዚህ ዘመቻ ፖለቲካዊ ወታደራዊ እና ድፕሎማሲያዊ ትርፍ ያገኘንበት ትልቅ ዘመቻ መሆኑን አረጋግጠናል። ለዚህ ዘመቻ መሳካት በሚድያውም በዘመቻውም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ድጋፍ ያደረጋችሁልን የትግላችን ደጋፊዎችም ከልብ እናመሰግናለን።

ዘመቻው ያማረ እና ከታቀደለት በላይ እንዲፈፀም በሞራል እንዲሁም በወኔ ተጋድሎ ላደረጋችሁ በሁሉም ቀጠና ለምትገኙ የፋኖ አባላት እና አመራሮችም ክብር ለናንተ ይሁን። ይህን ዘመቻ አንድነት የመጨረሻችን ባይሆንም መጀመሪያው ያማረ እና የተሳካ እንደነበር ሁላችንም ጠላትም ሳይቀር ያረጋገጠው ሃቅ ነው።

ይሁን እንጅ የአብይ አህመድ ደመ ጠጭ ጨፍጫፊ አረመኔ አገዛዝ እስከሚወድቅ እና እስትንፋሱ እሲኪጠፋ ድረስ ዘመቻችን የሚቀጥል ስለሆነ ሰራዊታችንን በቀጣይ አጠናክረን ለምናካሂደው ሁሉን አቀፍ ውጊያ ለግዳጅ ኦትሮል ዝግጁነቱን አጠናቆ እንዲጠባበቅ እያልሁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

1 የአሸናፊነት ስነልቦናችን የአጥቂነት መንፈሳችን ጠላትን የሚሰበረው ክንዳችን መሬት የማያርፈው ጥይታችን እንደጋለ መሆኑን በታላቅ ክብር እና ኩራት በሰራዊታችን ስም ለህዝባችን እና ለደጋፊዎቻችን ማሳወቅ እፈልጋለሁ።

2 አማራዊ አንድነት ግዴታችን መሆኑን ሁላችንም አምነንበት ስንሰራ የቆየን እና እየሰራን ያለ ሲሆን የድርጅታችንን ስያሜ እና አመራሩን በጥቂት ቀናት ይፋ እናደርጋለን።

3 ከሰፈር የፖለቲካ አስተሳሰብ የወጣ አማራን ነፃ የሚያወጣ እና ሃገሩን ኢትዮጵያን የሚጠብቅ አኩሪ ሰራዊት እንገነባለን።

4 የመዋቅር ማሻሻያ እና የኮር አደረጃጀት በመፍጠር ወቅቱን የሚመጥን የሰራዊት ግንባታ የምናደርግ ሲሆን የድስፕሊን ጥሰት ያለባቸውን አባላቶች በህጋችን መሰረት በክትትል እርምጃ በመውሰድ የምናስተካክል ይሆናል።

5 የመሪዎች የመኮነንነት ስልጠና በተጠናከረ መልኩ በማስቀጠል ህዝባችንን እና ሰራዊታችንን ለመምራት የሚያስችል አቅም እንገነባለን። ስለሆነም የድርጅታችን ወታደራዊ አመራሮች ቀጣይ ለሚኖራችሁ የመኮነንነት ኮርስ ራሳችሁን እንድታዘጋጁ ማሳሰብ እወዳለሁ።

ድል ለአማራ ህዝብ!
ድል ለፋኖ!

የአማራ ፋኖ በጎጃም ወታደራዊ አዛዥ

ሻለቃ ዝናቡ ልንገረው